## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

**በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የአምስቱ ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ኦዲት ሪፖርት**

ሚያዚያ 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


**ማውጫ** ........ I

**ክፍል አንድ** ........ 1

መግቢያ ........ 1

የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ተልዕኮ ፣ ራዕይ፣ ሥልጣንና ተግባር ........ 3

**ተልዕኮ** ........ 3

**ራዕይ** ........ 3

**የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስልጣንና ተግባር** ........ 3

**ድርጅታዊ መዋቅር** ........ 4

የሚኒስትር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 4

ለዝርዝር ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (AUDIT AREA) ........ 5

የኦዲቱ ዓላማ ........ 5

የኦዲት አካባቢ (AUDIT AREA) ........ 6

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ........ 6

**የመመዘኛ መስፈርቶች** ........ 6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 7

የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት እና አቅርቦት የስራ ሂደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) ........ 7

**ክፍል ሁለት** ........ 9

**የኦዲቱ ግኝቶች** ........ 9

ለከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የሚከናወኑ ጥናቶች ተግባራዊነታቸውን በተመለከተ፡- ........ 9

በከተሞች ለሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮክቶች ዝርዝር ዲዛይን በማከናወን ወደ ትግበራ የገቡ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 10

የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ የሚጠናቀቁ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 12

የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የኮንትራት አስተዳደርን በተመለከተ፡- ........ 14

የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች መረጣን በተመለከተ፡- ........ 17

የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የካሳ አከፋፈልን በተመለከተ፡- ........ 17

ሚ/ር መ/ቤቱ የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ስለመሆኑ፡- ........ 19

የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የሪፖርት ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፡- ........ 21

የከተሞች የመጠጥ ውሃ የፕሮጀክቶች ግዥ ሥርዓትን በተመለከተ፡- ........ 22

በከተሞች የሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የመሳሪያ እና የተለያዩ ንብረቶች ግዥ በውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ፡- ........ 24

የአቅም ግንባታ እንዲሁም የስልጠና ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፡- ........ 25

**ክፍል ሶስት** ........ 27

**የመደምደሚያ ሃሳቦች** ........ 27

**ክፍል አራት** ........ 30

**የማሻሻያ ሃሳቦች** ........ 30

**አባሪ- 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች** ........ 32

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች አንዱና ዋነኛው ንጽህ የመጠጥ ውሃ ነው፡፡ የተፈጥሮ ፍላጎትን ከማርካት ባሻገርም የንጽህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት የህብረተሰብን ጤንነት በመታደግ ለአገር ማህበራዊና የድህነት ቅነሳ (ኢኮኖሚያዊና ፖሊቲካዊ) የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡
2. በመሆኑም በኢትዮጵያ የውሃው ሀብት ልማት ስራ የተጀመረው የሃያኛው ምዕተ አመት ከመጀመሩ በፊት ባሉት ዓመታት ሲሆን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በሀገሪቱ በማስተዋወቅና በወቅቱ በነበሩ የአውሮፓ ሀገራት አምባሳደሮች በጐ ፈቃድ ነበር፡፡ በ1963 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የውሃ ሃብት ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮቹ ሸንጐ እንዲሆንና ውሃን በሀገሪቱ ዙሪያ ለእድገት መዋል እንዲቻል እውቅና ተሰጥቶት ተቋቋመ፡፡
3. በደርግ መንግስት ዘመን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት አገልግሎት ኃላፊነት የነበረበት መንግስታዊ አካል የውሃ ሃብት ኮሚሽን በተለይም በኮሚሽኑ ስር የነበረው የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ነበር፡፡ ይኸም ባለስልጣን መ/ቤት አገሪቱን በቀጠና በማከፋፈል የቀጠና ጽህፈት ቤቶችን አቋቁሞ አገልግሎት ለመስጠት ጽህፈት ቤቶቹ የጥናትና ድዛይን፣ የግንባታ፣ የቁጥጥርና ኦፐሬሽንና ጥገና ሥራዎችን ማዕከላዊ በሆነ መልኩ በተወሰነ ሰው ሃይልና ሎጅስትክ በየቀጠናቸው ባሉ አስተዳደሮች እየሄዱ አገልግሎት ይሰጡ ነበር፡፡
4. የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ኢሕአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣ ከ1983 ዓ.ም. በኋላ ደግሞ የተለያዩ ተቋማትን እንደገና የማደራጀቱ ስራ ተጀመረ፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀጽ 90 በማህበራዊ ነክ ዓላማዎች ንዑስ አንቀጽ አንድ፡ "የአገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣የንጹህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማህበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ያደርጋል" ተብሎ ተደነግጓል፡፡
5. የውሃውን ሴክተር የሽግግር ሥራ አስመልክቶ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ሚኒስትርና በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተለያይተው ይሰሩ የነበሩ ስራዎችን ወደ አንድ ቦታ በማምጣት የውሃ ሀብት ሚኒስቴር በ1987 ዓ.ም. እንዲመሠረት ተደረገ፡፡
6. መንግስት በቀጣዮቹ አምስት አመታት በሀገሪቱ ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጣውን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ተግባራዊ ባደረጉበት 2003 ዓ.ም. ደግሞ የውሃው

ሴክተር ዘርፍን ከኢነርጂ እይታ አንፃር ለያይቶ ማየት ስለማይቻልና በዕቅድ ዘመኑ የውሃና የኢነርጂ መስኩ ከፍተኛ እቅድ የተነደፈበት በመሆኑ የኢነርጂውን መስክ እንቅስቃሴ ከውሃው ሴክተር ጋር በሚኖርበት በአግባቡ መምራት እንዲቻል በአዋጅ ቁጥር 691/2003 ዓ.ም. የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በመባል እንደገና እንዲቋቋም ተደረገ፡፡ በ2008 በጀት አመት መጀመሪያ ላይ እንደገና በአዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም የውሃ፣ የመስኖና የኤሌክትሪክ ሚኒስቴር በመባል እንደገና ተዋቅሯል፡፡

7. ስለዚህ በመጀመሪያው የ5 ዓመት እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠውን ለማሳካት የከተሞችና ኢንዱስትሪዎች ፈጣን እድገት ጋር ተያይዞ የከተሞች ንጹህ መጠጥ ውሃ ፍላጎት በመጨመሩ አገልግሎት ያገኘውን ህዝብ ስታንዳርዱን ከፍ ለማድረገና በተሻለ ደረጃ አገልግሎቱን ኢንዲያገኝ ለማድረግና የተገነቡና እየተገነቡ የሚገኙ የውሃ ተቋማትን ዘላቂና አስተማማኝ አገልግሎት እንዲሰጡ የተቋማት አስተዳደር ስርዓትን ማጠናከርና ይህንን የሚያስፈጽም ተቋማዊ አደረጃጀት በየደረጃው ማቋቋምና ማጠናከር መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ያለው ጉዳይ ነው፡፡

8. የከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፕሮጄክት ለመጀመሪየው ጊዜ እ.ኤ.አ 2012 ወደ 2015 እንዲራዘም የተደረገበት በመጀመሪያው 100 ሚሊዮን አሜሪካ ዶላር ተጨማሪ 150 ሚሊዮን ዶላር በመገኘቱ ሲሆን ለፍሳሽ ሥራዎች ለአዲስ አበባ 100 ሚሊዮን ዶላር እና ለድሬደዋ የውሃን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ 50 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲመደብ ተደርጓል፡፡

9. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት ከIDA (Interanational Development association) በተገኘ ብድርና ዕርዳታ በተፈጸመ ስምምነት መሰረት ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማን የሚመለከተውን የከተማው ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት በቀጥታ ፤የአምስቱን ሁለተኛ ደረጃ ከተሞች ( መቀሌ፣ ጎንደር፣ ጅማ፣ ሐዋሳ እና ድሬደዋ) የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እና ሴኒቴሽን ፕሮጄክት ደግሞ በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር (የቀድሞው የውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር) በማስተባበር የሚያከናውን ነው፡፡ ፕሮጄክቱ

- የውሃ አቅርቦት መጠንን እና የፍሳሽ አወጋገድ ሥርዓትን ማሻሻል፣
- አነስተኛ ገቢ ላላቸው ህብረተሰብ ክፍል የተሻለ የውሃ አቅርቦትና የመጸዳጃ አገልግሎት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የከተሞች ውሃ አገልግሎት የአሰራር ቅልጥፍናና የፍላጎት አስተዳደርን ማሻሻል፣
- የውሃ ብክነትን የሚቀንሱ አሰራሮች እንዲኖሩ ማድረግ፣

- የከተሞችን ውሃ አገልግሎት አቅም መገንባት፣

የሚሉትን ሥራዎች ያካትታል፡፡

10. የአምስቱ ከተሞች ፕሮጀክትን አስመለክቶ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ዩኒት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን እንደሚጠበቅበት በፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ማንዋል (september 2012) ላይ ተጠቅሷል፡፡ ይህም፡-
    - ፕሮጄክቶቹን የማስተባበርና የማስተዳደር ሥራን ያከናውናል፤
    - በፕሮጀክቱ ሥር ለሚገኙ ፈጻሚዎች አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
    - ለፕሮጀክቱ ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ የሚ/ር መ/ቤቱ ዳይሬክቶሬቶች ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፤
    - ቀልጣፋ የፕሮጀክት ዕቅድና የአፈጻጸም ሥርዓት መዘርጋቱን ያረጋግጣል፤
    - የግዥ ሥራዎችን በማስተባበር የሚገዙ ንብረትና አገልግሎቶች በዕቅድ እንዲመሩ ያደርጋል፤ የሚዘጋጁ የግዥ ዕቅድና ሪፖርትን በመከለስ ግብረ መልስ ይሰጣል፤ እንዲሁም የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤

## የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ተልዕኮ ፣ ራዕይ፣ ሥልጣንና ተግባር

### ተልዕኮ

11. የውሃና የታዳሽ ኢነርጂ ሃብታችንን የአከባቢና የህብረተሰቡን ደህንነት በጠበቀ ሁኔታ በማልማት በዘላቂነትና በተቀናጀ መንገድ በማስተዳደር ዘርፉ ለሃገራችን ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ተገቢውን ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ፤

### ራዕይ

12. “በንፁህ መጠጥ ውሃ በመስኖና በታዳሽ ኃይል ልማት አቅርቦት አገራችን በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት የደረሱበትን ዕድገት አስመዝግባ ማየት”

## የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስልጣንና ተግባር

13. በአዋጅ ቁጥር 916/2008 የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል:-
    - የውሃ ሀብትና የኤሌክትሪክ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
    - የተፋሰስ ጥናት በማካሄድ የሀገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት አለኝታ በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

- ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ የግልጋሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይወስናል፣
- በወሰንና ወሰን ተሻጋሪ የውሃ አካላት አጠቃቀም ላይ ጥናት ያካሂዳል፣ አለም አቀፍ ውሎችን ይደራደራል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣
- የመካከለኛና የከፍተኛ መስኖ ልማት ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናት፣ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣
- ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት እንዲተላለፉ ካልተደረገ በስተቀር፣ በፌዴራል መንግሥት በጀት የተገነቡ ግድቦችንና የውሃ ውቅሮችን ያስተዳድራል፣
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች የሚውል ውሃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ ይወስናል፣
- የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ ያደርጋል፤ ከውጭ በሚገኝ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
- የሀገሪቱ ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲያድግና እንዲስፋፋ ያደርጋል፣
- የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ሥራ በአግባቡ እንዲከናወን መደረጉን ያረጋግጣል፡፡

## ድርጅታዊ መዋቅር

14. የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር በአንድ ሚኒስቴር እና በሁለት ሚኒስቴር ዴኤታዎች የሚመራ ሲሆን፤ በእነርሱ ሥር አንድ የአማካሪ ቡድን፣ አንድ ጽ/ቤት እና ሃያ ሰባት ዳይሬክትሬክቶች ተዋቅረዋል፡፡

## የሰው ኃይል

15. ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰውኃይል 1371 ሲሆን በ2007 የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት 878 የሰውኃይል በሥራ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም ውስጥ የሴት ብዛት 362 (41%) እና የወንድ ብዛት 516 (59%) ነው፡፡ አሁን ያለው የሰውኃይ በሙያ ሲተነተን ዶክትሬት1(0.1%)፣ማስትሬት 79 (9%)፣ ዲግሪ 186(21%)፣ ዲፕሎማ 141(17%) እና ሰርቴፊኬት 471(54%) ናቸው፡፡

## የሚኒስትር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

16. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ብድር፣እርዳታና ከመንግስት፣ የሚመደብለት በጀት ሲሆን፣ የሚ/መ/ቤቱ የፋይናንስ መረጃ እንደሚያመላክተው ከ2005 እስከ 2007 ዓ.ም የተፈቀደ (የተመደበ) በጀት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| በጀት ዓመት | የተመደበ በጀት | | | ሥራ ላይ የዋለ በጀት (እስከ ታህሳስ 30/2008 ዓ.ም) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | መደበኛ | ካፒታል | ድምር | መደበኛ | ካፒታል | ድምር |
| 2005 | 56,311,000.00 | 3,005,739,500.00 | 3,062,050,500.00 | 45,233,238.64 | 3,099,775,404.20 | 3,145,008,642.84 |
| 2006 | 75,678,750.03 | 3,301,595,476.50 | 3,377,274,226.53 | 63,868,983.58 | 4,046,589,303.75 | 4,110,458,287.33 |
| 2007 | 69,032,047.14 | 3,100,000,350 | 3,169,032,397.14 | 62,824,701.14 | 3,020,414,234.49 | 3,083,238,935.63 |
| 2008 | 287,498,673.49 | 2,874,805,230.00 | 3,162,303,903.49 | 188,860,997.06 | 709,830,879.73 | 898,691,876.79 |

የፕሮጀክቶች የእርዳታና ብድር ከ2005 እስከ 2007 ዓ.ም በኢትዮጵያ ብር

| በጀት ዓመት | የተመደበ በጀት | | | ሥራ ላይ የዋለ በጀት (እስከ ሰኔ 30/2007 ዓ›ም) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብድር | ዕርዳታ | ድምር | ብድር | ዕርዳታ | ድምር |
| 2005 | 384,808,000.00 | 1,033,000,000.00 | 1,417,808,000.00 | 110,591,098.00 | 415,969,626.00 | 526,560,724.00 |
| 2006 | 241,264,800.00 | 800,000,000.00 | 1,041,264,800.00 | 63,542,341.00 | 700,057,992.00 | 763,600,333.00 |
| 2007 | 800,000,580.00 | 400,001,490.00 | 1,200,002,070.00 | 514,573,072.00 | 31,110,522.00 | 545, 683, 594 |

## ለዝርዝር ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

17. በሚኒስቴር መሰሪያ ቤቱ ከሚገኙ የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ውስጥ፣ "የ5 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት (Secondary cities) (በግንባታ ላይ ያሉ)"፣ አፈጻጸምን የተመለከተ ነው፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

18. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የውሃ፣መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀምን አስመልክቶ ለክልሎች የሚያደርገውን እገዛ፤ ከውጭ የሚገኘውን እርዳታና ብድር በአግባቡ ለፕሮጀክቱ መስፈፀሚያ መዋሉን የመከታተል ፣ የማስተባበር እንዲሁም ድጋፍና ክትትል የማድረጉን ስራ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን፣ ሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር እንዲሁም በክልሎች መካከል የእርስ በእርስ ትስስር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን የሚያመቻች፣ እገዛ የሚያደርግና የሚከታተል መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚያግዙ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

19. ከከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ውስጥ የአምስት ከተሞች (መቐለ፣ ሀዋሳ፣ ድሬደዋ፣ ጅማ እና ጎንደር) የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት (secondary cities) አፈፃፀምን በተመለከተ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለክልሎች የሚያደርገውን እገዛ፤ ከውጭ የሚገኘውን እርዳታና ብድር በአግባቡ ለፕሮጀክቱ መስፈፀሚያ መዋሉን የመከታተል ፣ የማስተባበር እንዲሁም ድጋፍና ክትትል ማድረጉን፣ ስራ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች

### የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

20. ይህን የኦዲት አካባቢ ኦዲት ለማድረግ ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም፥

1. የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት ዝግጅት መርሃ-ግብር፣ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ አሰራር ስርአት የተዘረጋለትና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ማጣራት፣
2. ለከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዋና ፈጻሚ ከሆኑ ባለድርሻ (የክልል ቢሮዎች፣የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር፣) አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ስርአት የተዘረጋለት እና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ማጣራት፣
3. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፤የከተማ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ፅ/ቤቶች በስራቸው የሚከናወኑ የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የባለሙያ አማካሪና የኮንትራክተር አገልግሎት ግዥ፣ የእቃና የመሳሪያዎች አቅርቦት ግዥ በመንግስት ግዥ መመሪያ፤በአለም ባንክ የግዥ መመሪያ መሰረት እና በግዥ ውል መሰረት መፈፀማቸውን ማጣራት፣

### የመመዘኛ መስፈርቶች

21. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 30 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ሚ/ር መ/ቤቱ የተቋቋመበት አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች፣ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የአምስት ዓመት ስትራቴጂ

ዕቅድ/ከ2003-2007/፣ ከ2005-2007 ዓ.ም ድረስ ያሉ መፅሄቶች እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ፣ ሊሆን የሚችል መደምደሚያ (likely conclusions)፣ ከኦዲቱ የሚጠበቁ የማሻሻያ ሀሳቦች (expected recommendations)፣ ኦዲቱ የሚከናወንበት ዘዴዎች (audit methodologies)፣ ለኦዲቱ የሚፈለጉ መረጃዎች እና የሚገኙበትን አካባቢ የሚያሳዩ መግለጫዎች ተዘጋጅተው ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

22. ኦዲቱ የሚሸፍነው አጠቃላይ የፕሮጀክቱን አፈጻጸምን ሆኖ በዋነኛነት ከ2005 በጀት ዓመት እስከ 2007 በጀት አመት የአምስቱ ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈጻጸመን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎችን ነው፡፡ ኦዲቱ በዋነኝነት የሚከናወነው በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ሲሆን፣ ከክልል ከተሞች የውሃ አገልግሎቶች እና ከውሃ ፈንድ ልማት ጽ/ቤት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብ እንዲሁም ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ ነው፡፡ በከተሞች በግንባታ ላይ ያሉ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ብዛት 5 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ ሶስቱ (አዲስ አበባ፣ ድሬደዋና ሀዋሳ) ለኦዲት በናሙና ተመርጠ በኦዲቱ ታይተዋል፡፡

## የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት እና አቅርቦት የስራ ሂደት መግለጫ (process description)

23. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን ለመስጠት በመጀመሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍላጎት የመነጩ እቅዶች/ፕሮግራሞችን መሰረት በማድረግ ረቂቅ እቅድ አዘጋጅቶና በረቂቅ እቅዱ ላይ አስተያየት እና ማሻሻያዎችን አካቶ በመ/ቤት ደረጃ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት እቅድ ካዘጋጀ በኋላ ክልሎች ፕሮፖዛል እንዲያቀርቡ ጥሪ ያቀርባል። በቀረበላቸው ጥሪ መሰረት ክልሎች ፕሮፖዛል ካላቀረቡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በራሱ የሚያቀርብበትን አማራጭ ይፈልጋል። ክልሎች ጥሪውን ተከትለው ፕሮፖዛሎችን ካቀረቡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮፖዛሎቹን ይከልሳል። ፕሮፖዛሎቹ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተቀባይነት ሳያገኙ ከቀሩ ለክልሎቹ መመለስ እንዲሁም ተቀባይነት ካገኙ ለፕሮፖዛሎቹ ቅደም ተከተል መስጠት ፣ በቅደም ተከተላቸው መሰረት ፋይናንሰሮችን ለይቶ ማሳመን፣ ፕሮፖዛሎቹን ለፋይናንሰሮች ማቅረብ እና የውል ሰነድ በማዘጋጀት ስምምነት መፈራረምን ያከናውናል። ስምምነቱ ከተፈረመ

በኋላ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፕግራሞቹ/ፕሮጀክቶቹ ፈንድ በወቅቱ ማስለቀቅ፣ በቴክኒካልና ፋይናንሻል አፈጻጸም ዙሪያ ድጋፍ መስጠት፣ ለአፈፃፀም የሚረዱ መመሪያና ደንቦችን ማዘጋጀት እና አፈጻጸማቸውን መከታተል፣ የቴክኒክ ድጋፍና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን እንዲሁም ከስራው ጋር አግባብነት ያላቸውን አካላትን በማስተባበር የፕሮግራሞቹን/ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ያግዛል። የስራዎችን መገባደድ ተከትሎም የማጠቃለያ ሪፖርት ያዘጋጃል።

24. ክልሎች እና የከተማ መስተዳድሮች በበኩላቸው የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን ለህብረተሰቡ ለማድረስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተቀባይነት ላገኙ ፕሮፖዛሎች ጥናትና ዲዛይን መስራት፣ ለፕሮጀክቶች ግንባታና አስተዳደር ጥናት እና ዲዛይን ማከናወን፣ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶቹ የሚገነቡበት ንጹህ የመጠጥ ውሀ ምንጭ ከከርሰ ምድር እና ገፀ ምድር መምረጥ፣ በፕሮጀክቶች ጥናት መሰረት ለግንባታ የስራ መግለጫ (term of reference) ማዘጋጀት፣ አማካሪ/ኮንትራክተር መቅጠር፣ የፕሮጀክቶች ግንባታ ስራ ላይ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ፣ ግንባታዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ርክክብ መፈፀም እንዲሁም ግንባታዎች አግልግሎት ላይ ከዋሉ በኋላ የኦፕሬሽን እና ጥገና ስራ፣ የውሀ ጥራት እና ቁጥጥር እንዲሁም የሲቪልና የኤሌክትሮሜካኒካል ስራ በማከናወን ፕሮጀክቶችን ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል።

# ክፍል ሁለት

## የኦዲቱ ግኝቶች

### ለከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የሚከናወኑ ጥናቶች ተግባራዊነታቸውን በተመለከተ፡-

25. ለከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ትግበራ የፕሮጀክት የአዋጭነት Feasibility study)፣ ፕሮጀክቶች ለምን ያህል ጊዜ (project time) እና ህዝብ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው የሚያመለክት ጥናት ሊከናወን ይገባል፡፡ በጥናቱም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ከመጀመራቸው በፊት የውሃ መገኛ ቦታዎች፣ ቁፋሮ የሚካሄድባቸው ቦታዎች በቂ፣ ቀጣይነት እና አስተማማኝ የመጠጥ ውሃ ያላቸው መሆናቸው፣ ፕሮጀክቱ ለምን ያህል ጊዜ እና ለምን ያህል ህዝብ አገልግሎት መስጠት እንደሚችል፣ ፕሮጀክቱ የሚፈጥረው አካባቢ ተፅዕኖ እና ሌሎች ጉዳዮች ጥናት ውስጥ የሚካተቱ ቢሆንም

27. የውሃ ፕሮጀክቶቹ

- የሚያደርሱትን የአካባቢ ተጽዕኖ፣ ከጥራትም ሆነ ከብዛት አንፃር ለመገምገም የሚያስችል ተስማሚ የአሰራር ቅደም ተከተልና የአጠናን ዘዴ በመቅረጽ የአካባቢ እንክብካቤ ጥናት ከውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ በፊትም ሆነ በኃላ ማካሄድ አለመቻሉን፣
- የጎንደር ከተማ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ውሃ አለባቸው ተብሎ የተመረጡ ቦታዎች ላይ ውሃ አለመገኘቱ፣ አሁንም ለፕሮጀክቱ የተመረጡት የውሃ ምንጮች (አንገረብ እና ቆላድባ) በጥናቱ ላይ በተቀመጠው መሰረት የከተማውን የውሃ ፍላጎት እስከ 2020 ድረስ እንኳን መሟላት የማይችሉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. ስለ ሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ የ5ቱ ከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ብዙ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የነበሩት መሆኑን፣ በተለይ እነኚህ ከተሞች ከአ/አበባ ልምድ እንዲወስዱ ታስቦ ስራው የተጀመረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የአዋጭነት ጥናት በረጅምና በመካከለኛ ጊዜ ተከፍሎ (የአካባቢ ተጽዕኖና ማህበራዊ ጉዳዮች አዋጭነት ጥናት ውስጥ ተካቶ የተሰሩ እና ጥናቱ ደግሞ የፕሮጀክቱ አካል መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ፕሮጀክቱ ለምን

ያህል ህዝብ አገልግሎት መስጠት እንዳለበት ከፍላጎት አንፃር የሚታይ በመሆኑ የውሃ ፍላጎት እና አቅርቦት የማይጣጣም መሆኑን እንዲሁም የድሬዳዋ ጉዳይ በቁጥሮች ልዩነት የተፈጠረ እና ብዙን ጊዜ ከስታትስቲክስ የሚወሰድ ስለሆነ የህዝብ ብዛት ቁጥር በየጊዜው የሚቀያየር መሆኑን በአጠቃላይ የአማካሪዎች አቅም ውስንነት ጋርም የሚያያዝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የጎንደር ከተማ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክትን በተመለከተ የከርሰ ምድር ውሃ ጥናት "Success" በመልክአ ምድር ሁኔታ፣ የጥናት መሳሪያዎች እጥረትና ዘመናዊነት እንዲሁም የባለሙያዎች ክህሎትና ልምድ ላይ የተመሰረተ መሆኑን እና በኢትዮጵያ የጉድጓድ "Success Rate" ከ70% የማያልፍ መሆኑን፤ የገለጹ ሲሆን የጎንደር ከተማ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በተመለከተ በፕሮጀክቱ ዘጠኝ ነባር ጉድጓዶችን በማደስ እና የውሃ ብክነትን ከአለበት ከ28% ወደ 20% ከመቶ በመቀነስ የተገኘውን ውሃ ጨምሮ በ2020 ከከተማው የውሃ ፍላጎት በላይ ለማምረት መታቀዱን ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በቆላ ድባ በተቆፈሩት 8(ስምንት) ጉድጓዶች ከ234.5 l/s ውሃ መገኘት መቻሉን ኃላፊዎቹ ቢገልጹም ጥናቱ ላይ ውሃ ይገኛል የተባለበት ቦታ ከገንዘብ እጥረት ጋር ስለማይገናኝ፣ ለከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ትግበራ የአዋጭነት ጥናት Feasibility study) ሲጠና ፕሮጀክቶች ለምን ያህል ጊዜ (project time) እና ህዝብ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው ማመላከት ስላለበትና በዚሁ መሰረት ጥናቱ ተግባራዊ መደረግ ስላለበት የሰጡትን ምክንያት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

29. ለከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ትግበራ የፕሮጀክት የአዋጭነት Feasibility study)፣ ፕሮጀክቶች ለምን ያህል ጊዜ (project time) እና ህዝብ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው የሚያመለክት ጥናት ተግባራዊ አለመደረጉ የውሃ አገልግሎቶቹ ለጥናቱ ያወጡት ወጪ እንዲባክን ከማድረጉም በላይ የቦታዎቹ፣ የተጠቃሚዎቹ እንዲሁም በአጠቃላይ ጥናቱ መቀያየሩ የውሃ አገልግሎቶቹን ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋቸዋል፡፡

## በከተሞች ለሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮክቶች ዝርዝር ዲዛይን በማከናወን ወደ ትግበራ የገቡ መሆኑን በተመለከተ፡-

30. በከተሞች የሚገኙ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች፣ ጥናትና ዲዛይን ተጠናቆ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግሞ በዚሁ መሰረት ሥራው ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

31. ይሁን እንጂ በሀዋሳ ከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጄክት የውሃ ፓወር ፓምፕ ፕላንት (Power pump plant) መጀመሪያ ይገነባል ከተባለበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የተቀየረ መሆኑን፣ በሀዋሳ በሲቪል ሥራ የሚከናወነው ለሃዋሳ ከተማ የውሃ አገልግሎት የቢሮ ህንጻ ግንባታ ዲዛይን ለውጥ በመደረጉ 52 ሚሊዮን ብር የተያዘለትን ወደ 62 ሚሊዮን ብር እንዲቀየር መደረጉን እንዲሁም የመጀመሪያውም ሆነ የተከለሰው ዲዘይን የመኪና ማቆሚያ፣ የግቢ ጽዳት እና የአጥር ሥራን ያላካተተ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እንዲሁም ለሀዋሳ ከተማ ውሃ አገልግሎት ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

32. የድሬዳዋ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የኤሌክትሮሜካኒካል ዕቃዎች አቅርቦትና ተከላ ዲዛይን በአማካሪው ድርጅት ክለሳ ተደርጎበት ከታህሳስ 2007 ዓ.ም ጀምሮ የተከለሰው ዲዛይን ግምገማ አድርጎ የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ሂደቱ እስከ መስከረም 30 2008 ዓ.ም ድረስ የዲዛይን ማስተካከያ ሥራ ላይ የነበረ መሆኑን እንዲሁም ዲዛይኑ በመገምገም እና የሚፈለገውን ግብረ-መልስ በመስጠት እና በማጽደቅ በፍጥነት ወደ ሥራ እንዲገባ ባለመደረጉ ሥራው ላይ መጓተት አስከትሏል፡፡ በተጨማሪም የአምስቱ ከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ግንባታው በተጠናው ጥናትና ዲዛይን መሰረት እየተከናወነ ስለመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ ባለሙያ በመመደብ በየደረጃው ቋሚ ክትትል ማድረግ አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በኦዲቱ ወቅት ተመርጠው በናሙና ከታዩ የውሃ አገልግሎቶች ከተደረገላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

33. በኦዲቱ ወቅት የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤የተለያዩ ቦታዎች የመስመር መቀየር ችግር መሆኑን፣ ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች በመጀመሪያ ከጥናቱ የሚጀምርና ጥናቱ የተሟላ መሆኑ ጋር የሚያያዝ መሆኑን፣ በዲዛይን ክለሳ ጊዜ የሚቀነሱም የሚጨመሩም ጉዳዮች ሊኖሩ እንደሚችሉ፣ ሀዋሳ ውሃ አገልግሎትም ድዛይን ክለሳ ያደረገው የራሱን ፍላጎት ለማሳደግ ብሎ መሆኑን፣ ውሃ መገኛ ቦታዎች በተመለከተ ጥናት ሲካሄድ ውሃ መገኛ ቦታ ተብሎ የሚመረጡ ቦታዎች ውሃ መኖራቸውን መቶ ፐርሰንት እርግጠኛ መሆን አለመቻሉን ስለዚህ ብዙን ጊዜ ሳይት/ቦታዎች ከተቀየሩ ድዛይንም ለመቀየር የሚገደድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ውሃው ተገኝቶ ጥናት ቢሰራና የጉድጓድ ቁፋሮን የጥናት አካል ቢሆን ጥሩ መሆኑን ነገር ግን ብዙ ገንዘብ ስለሚፈጅ ፕሮጀክቶቹ በዚህ መልኩ የማያከናውኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

34. እንዲሁም የድሬዳዋ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የኤሌክትሮሜካኒካል ዕቃዎች አቅርቦትና ተከላ ዲዛይንን በተመለከተ የአማካሪው አቅም ውስንነት መኖሩን እና ፕሮጀክቱ ትልቅ ከመሆኑ አንፃር ከውሃ አገልግሎት እና ከአማካሪው መካከል ብዙን ጊዜ ልዩነት በመፍጠር ሊግባቡ ባለመቻላቸው ረጅም ጊዜ ለመውሰዱ አንዱ ምክንያት የነበረ በመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ በማስታረቅ እና በመደገፍ አሁን በደረሰበት ደረጃ እንድደርስ አድርጎ ጨረታ ሂደት ላይ ማድረሱን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም የህዝብ ብዛት መረጃ እንደ ምንጩ የሚለያይ ሲሆን በድሬዳዋ በበጀት እጥረት የተወሰኑ ሥራዎች እንዲቀነሱ በመደረጉ የተጠቃሚው ቁጥር በዚያው መሰረት ስለተስተካከለ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ጥናት ሲጠና ሚፈለገው የውሃ መጠን መኖሩ መረጋገጥ ስለሚገባው ዲዛይን ሲሰራ መካተት የሚገባቸው ዋና ዋና ሥራዎች መካተት ስለነበረባቸውና የሥራ ተቋራጭ ሆነ አማካሪ ፈቃድ ሲሰጠውም ሆነ ለሥራ ሲመረጥ ብቃት ያለው መሆኑ መረጋገጥ ስለሚገባው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

35. በከተሞች የሚገኙ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች፣ ጥናትና ዲዛይን ተጠናቆ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግሞ በዚሁ መሰረት ሥራው ተግባራዊ አለመደረጉ ዲዛይኑ እንዲቀያየር በማድረግ ለተጨማሪ ወጪ ከመዳረጉም በላይ ለሙስና (ገንዘብን አለአግባብ ለመጠቀም) በር ይከፍታል፡፡

## የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ የሚጠናቀቁ መሆኑን በተመለከተ፡-

36. ሚ/ር መ/ቤቱ ከውጭ በሚገኝ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ መከታተልና ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

37. የአምስቱ ከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት በብድር እና ዕርዳታ ስምምነት እ.ኤ.አ በ2007 ተጀምሮ በ2012 ለማጠናቀቅ በአለም አቀፍ ልማት ማህበር (IDA) ጋር የብድር እና የእርዳታ ስምምነት የተፈረመ እና የስምምነት ጊዜው ሲልያቅ እ.ኤ.አ. ከ2013-2015 ለማራዘም ተጨማሪ የብድር እና የእርዳታ ስምምነት መፈረሙ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ በሁሉቱም ስምምነቶች የተያዙ ስራዎቸ በተያዘላቸው የጊዜ ገድብ ያልተጠናቀቁ በመሆኑ ተጨማሪ ጊዜ እስከ ታህሳስ 2016 ድረስ ለተጨማሪ አንድ አመት እንዲራዘም ተደርጓል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ተመርጠው የታዩ ከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ያሉት ቀሪ ሥራዎች በቀሪው ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንደማይችሉ የገለጹ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀሪው ጊዜ የፕሮጀክቱ ሥራዎች

እንዲጠናቀቁ ውጤታቸው በተጨባጭ ሊደረስበት የሚችለውን ተፈፃሚነት ያለው ቁጥጥር እና ክትትል ስርዓት በመዘርጋት የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም መከታተል አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

38. ለድሬደዋ ከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ከሚከናወኑ ሥራዎች አንዱ የነበረው የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ በውሉ መሰረት በስድስት ወራት ውስጥ መጠናቀቅ ሲገባው በጊዜው ባለመጠናቀቁ ለተጨማሪ ስድስት ወራት (ከseptember 13/2013 to march 18/2014) እንዲራዘም ቢደረግም ከአንድ አመት ስራ በኋላ አፈጻጸሙ ከ20% በታች በመሆኑ ኮንትራቱ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ አዲስ ጨረታ ወጥቶ ሥራው ሲጂሲ ለተሰኘ ሌላ ኮንትራክተር በአራት ወራት እንዲጠናቀቅ ውል ከተገባ በኋላ ሥራውን በተባለው ጊዜ ማጠናቀቅ አለመቻሉንና 11 ወራት መፍጀቱ ታውቋል፡፡ የፕሮጀክት የኤሌክትሮሜካኒካል ስራ፣ የአንድ ሪዘርቫየር ግንባታ (ሳቢያን አከባቢ) እና በአነስተኛ ገቢ ለሚኖሩ ህብረተሰብ (LIA) የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ለመስጠት ገና ጥናት ላይ በመሆኑ ሥራ አለመጀመሩን አጠቃላይ የፕሮጀክቱ 43% ላይ መሆኑን ታውቋል፡፡

39. የጎንደር ከተማ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት በ2008 በጀት ዓመት 1ኛ ሩብ ዓመት መጨረሻ የፕሮጄክቱን 4.28% ለማከናወን ታቅዶ 1.2% (የዕቅዱን 28%) ማከናወን በመቻሉ አጠቃላይ አፈጻጸሙ 82.62% መደረሱን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሰ የበጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

40. እንዲሁም በሀዋሳ የውሃ አገልግሎቱ ቢሮ የሚሆን የህንጻ ግንባታ ውል ማሻሻያ ፌብሪዋሪ 16 2015 የተደረገ ሲሆን ዲዛይን ለውጥም (የህንጻው አንደኛ ወገን ጂ+3 የነበረውን ወደ ጂ+4፣ የሌላኛው ወገን ጂ+1 የነበረው ወደ ጂ+3 እንዲቀየር ተደርጎ) ብር 51,566,748.87 የነበረው 10,836,449.46 ተጨምሮ ወደ ብር 62,403,198.33 ከፍ ብሏል (ውሉ ሌሎችን የፕሮጄክቱን የሲቪል ግንባታ ሥራዎችን ይጨምራል)፡፡ የማጠናቀቂያ ጊዜውም ወደ ሜይ 30, 2015 እንዲሆን ስምምነት ተገብቶ (ሁለት ዓመት ያህል እንዲራዘም ተደርጎ) እስከ አሁን የህንጻው ግንባታ አለመጠናቀቁን፣ የአጥር እና የፓርኪንግ ግንባታ ስራ ከህንፃ ግንባታ ውል ውጪ በመሆኑ ያልተሰሩና ለማሰራትም ጨረታ አለመውጣቱ እና ባለ 4000 ኪቢዩክ ሜትር የውሃ ማጠራቀሚያ ሪዘርቫየር ግንባታ ጨረታው ገና ያልወጣ መሆኑን እና አጠቃላይ የፕሮጀክቱ አፈፃፀም 65% ላይ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የውኃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. ስለ ሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ትክክል መሆናቸውን፣ እስካሁን ድረስ የሀዋሳ፣ የመቀሌ ፌዝ አንድ እና የጅማ ከተማ ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን፣ የመጀመሪያው ተጨማሪ ፋይናንስንግ ስምምነት የተደረገው 1ኛ- በመጀመሪያ በፕሮግራሙ የተቀመጡ ዓላመዎች ጋር መድረስ የማይችሉ ከተሞች በመኖራቸው 2ኛ-የፍሳሽ አገልግሎት እንዲካተት በመደረጉ 3ኛ- የሀዋሳንና የአዲስ አበባን አቅም ለማሳደግና የድሬዳዋን ለማካተት ስለነበር መሆኑን፣ አንድ ዓመት የተራዘመው የድሬዳዋና የአዲስ አበባን ግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን ከድሬዳዋ በስተቀር ሌሎች በቀሪው ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃሉ ብለው እንደሚያስቡ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ድሬዳዋ የሳቢያን አካባቢው የሚሰራው ካሳ ጉዳዩ አልቆ የሪዘርቫየር ግንባታ መጀመሩን፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው አካበበዊዎች እና የውሃ ብክነት ቅነሳ ጥናቱ መጠናቀቁን፣ የሀዋሳ የውሃ አገልግሎቱ የህንጻ አጥርና የመኪና ማቆሚያ ግንባታ ጨረታቸው ተጠናቆ አሁን ግንባታ መጀመሩን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ፕሮጀክቶቹ ወቅታቸውን ጠብቀው መጠናቀቅ ስላለባቸውና አብዛኛው ገንዘብ የተገኘው በብድር በመሆኑ እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶቹ በተባለላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ የክትትል እና ድጋፍ የማድረግ ሥራ የሚጠበቅበት በመሆኑ ያቀረቡትንምክንያት ለመቀበል ያዳግታል፡፡

42. ሚ/ር መ/ቤቱ ከውጭ በሚገኝ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ድጋፍ አለማድረጉ ፕሮጀክቶቹ በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ እንዳይጠናቀቁ ከማድረጉም በላይ በህብረተሰቡ ዘንድ ወቅቱን የጠበቀ ጥቅም እንዳይሰጡና የውሃ አገልግሎቶቹን የውሃ አቅርቦት ተደራሽነት አፈጻጸም እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

## የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የኮንትራት አስተዳደርን በተመለከተ፡-

43. የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ኮንትራት አስተዳደር በተገባው የኮንትራት ውል ስምምነት መሰረት ሊፈጸም ይገባል፡፡ የከተማ ውሃ አገልግሎቶቹም ሆኑ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራዎች በተባለላቸው ጊዜና በጀት መጠናቀቃቸውን የቅርብ ክትትል በማድረግ ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡

44. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኮንትራክተሮች የፕሮጀክት አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም ብቁ የሆነ የፕሮጀክት አስተዳደር አለመኖር ለፕሮጀክቶች ፋይናንሻል

አጠቃቀሙ ዝቅተኛ መሆኑን፣ ሥራ ተቋራጮች ውል ከፈጸሙ በኃላ ቶሎ ወደ ስራ አለመግባትና ጊዜ እንዲራዘምላቸው መጠየቅ ሁኔታ መኖሩ ታውቋል፡፡

45. ይህም በጎንደር ለአማራ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት (AWWCE) and Al-Nile business group በውል የተሰጠ የጉድጓድ ቁፋሮ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ የዘገየ ቢሆንም በውሉ መሠረት እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉን፣ በመቀሌ ከተማ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ኢዩሮፓ ጀነራል ትሬድንግ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባኒያ ለውሃ ሜትር እና ስፔር ፓርቶች አቅርቦት እ.ኤ.አ በግንቦት 22 ቀን 2010 እንዲያልቅ በኮንትራት ውል የተገባ ሲሆን ስራው ያለቀው እ.ኤ.አ መስከረም 16 ቀን 2010 ሲሆን ወደ 4 ወር የዘገየ መሆኑ፤ (የውሃ ሜትር ቴስት ቤንች ለማቅረብ የተገባው የማጠቃለያ ጊዜ እ.ኤ.አ ግንቦት 25 ቀን 2011 ሲሆን ስራው ያለቀው እ.ኤ.አ በሀምሌ 23 ቀን 2011 ሲሆን ከኮንትራቱ የዘገየው 2 ወር መሆኑ እና ለካርጎ ትራክ እና ክሬን ለማቅረብ በውል የተገባው ማጠቃለያ ጊዜ እ.ኤ.አ ሰኔ 1 ቀን 2011 ሲሆን ከተያዘው ቀን ሁለት ወር ዘገይቶ ማቅረቡ፤) እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከተያዘላቸው ዕቅድ በታች መሆኑን ታውቋል፡፡

46. በድሬዳዋ ከተማ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ጣና ድሪሊንግ የጥልቅ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ለማከናወን ለስድስት ወራት ተሰጥቶ በጊዜው ባለመጠናቀቁ ለተጨማሪ ስድስት ወራት (ከseptember 13/2013 to march 18/2014) እንዲራዘም ቢደረግም አፈጻጸሙ ከ20% በታች በመሆኑ ኮንትራቱ እንዲቋረጥ ተደርጎ ሲጂሲ የሚባል የቻይና ኩባኒያ ጨረታውን አሸንፎ ኮንትራት ውል ቢፈርምም ተቋራጩ ውል በሚፈርምበት ወቅት ያሉት ለስራው የሚያስፈልጉት ግብዓቶች፡ ሰው ሃይልና ማሽነሪ ከዚህ ቀደም በተፈጸመ የኮንትራት ስራ ተይዘው ስለሚገኙ በወቅቱ ሥራውን አለመጀመሩ በተያዘው ጊዜ ገደብ (3 ወር) ውስጥ ስራውን ማጠናቀቅ ባለመቻሉ ተጨማሪ የ3 ወር ጊዜ ቢሰጥም ማጠናቀቅ ባለመቻሉ በኮንትራት ውሉ መሰረት 1.9 ሚሊዮን ብር ቢቀጣም በአጠቃላይ የቁፋሮ ስራ መዘገየት ምክንያት የፕሮጀክቱ የኤሌክትሮሜካኒካል ግዥ አንድ አመት ከ6 ወር በላይ እንዲዘገይ ማድረጉን እና በድሬዳዋ ከተማ ፕሮጀክት ጣና ድሪሊንግ ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ በገባው የኮንትራት ውል መሰረት ሥራውን ባለመጠናቀቁ እና ውሉ በመቋረጡ የተወሰደው እርምጃ ፍትሃዊ አይደለም በሚል ኮንትራክተሩ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወስዶ የፍትህ ሂደቱ እስካሁን ስለ አለመጠናቀቁን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የድሬደዋ ከተማ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ዩኒት ለማወቅ ተችሏል፡፡

47. በአጠቃላይ ሥራውን በውላቸው መሰረት በማያከናውኑ ተቋራጮች ላይ የድሬዳዋ ከተማ ውሃ አገልግሎት ሲ.ጂ.ሲ. የተባለው ኮንትራክተር ላይ ከወሰደው የክፍያ ቅጣት በስተቀር በውሉ መሰረት አስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ሪፖርቶች እና በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የከተማ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶችና ከተከለሱ ሰነዶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

48. ስለ ሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ እንደ ሀገር ኮንትራት አስተዳደር አቅም አናሳ መሆኑን፣ የስራ ተቋራጮችና የአማካሪዎች አቅም ማነስ፣ ኮንትራክተሮች በብዛት ቢኖሩም አቅም ያለው ኮንትራክተር በብዛት አለመኖሩን፣ የማስፈፀምና የሰው ሃይል አቅም ውስንነት እንዲሁም አመካሪዎች የገንዘብ እና ልምድ ያለው የሰው ሀይል አቅም ውስንነት መኖሩን፣ ጨረታ ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችም አማካሪዎች ጥናት ወደ ጨረታ ሰነድ ስለሚገባ ችግር መፍጠሩን እንዲሁም በወረቀት ላይ የሚቀመጡ እንደ ማባረር፣ መቅጣት እርምጃዎች ሊወሰዱ እንደሚችሉ እና ሙከራም ማድረጋቸውን፣ ይሁን እንጂ ሁሉም ኮንትራክተሮች አቅም ስለሌላቸው ማንን አባሮ ማንን ማስቀጠል የሚለው አስቸጋሪ በመሆኑ ኮንትራክተሮቹ በተለያየ መንገዶች ስራቸውን እንዲያጠናቅቁ የሚያደርጉ መሆናቸውን እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በውሉ ውስጥ በተቀመጠው አንቀጾች መሰረት፤ ውሉን አቋርጠው አዲስ ጨረታ ውስጥ መግባት የሚያዋጣ ሆኖ ከተገኘ፣ ተጨማሪ ሥራዎች ከተጨመሩ፣ በሀገሪቱ የግንባታ ግብዕቶች ችግር፣ የL/C የመክፈት ሂደቶች መዘግየት ምክንያቶች ኮንትራቶች እንዲራዘሙ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ከተሞቹ ራሳቸው የግዥ ባለሙያ መቅጠር ያለባቸው ቢሆንም ከድሬዳዋ እና ከጎንደር ከተሞች ውሃ አገልግሎቶች በስተቀር ሌሎቹ ባለመቅጠራቸው ኮንትራክቱን ማስተዳደር ላይ የራሱን ተጽዕኖ መፍጠሩን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ መጀመሪ የሥራ ተቋራጭም ሆነ የአማካሪ መረጣ ሲካሄድ ሁኔታዎቹን ከግምት ውስጥ ማስገባት ስለነበረባቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

49. የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ኮንትራት አስተዳደር በተገባው የኮንትራት ውል ስምምነት መሰረት አለመሆኑ እና ሚ/ር መ/ቤቱ በኮንትራት ውል መሰረት ለማያከናውኑ ኮንትራክተሮች ህጋዊ እርምጃ አለመውሰዱ ፕሮጀክቱ በታቀደለት ጊዜ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት እንዳይጀምር አድርጎቷል፡፡

## የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች መረጣን በተመለከተ፡-

50. ሚ/ር መ/ቤቱ ለመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች መረጣ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ተፈላጊውን የሰው ኃይል እና አስፈላጊ መሣሪያዎች ያላቸውን እና ሥራቸውን በገቡት ውል ላይ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ መሰረት ማጠናቀቅ የሚችሉትን ተቋራጮችን በማረጋገጥ ሊመረጡ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ በሥራ ተቋራጮች በኩል ሁሉንም ቅድመ ሁኔታ እናሟላለን ብለው ጨረታ አሸንፈው ውል ከገቡ በኋላ አሟልተናል ያሉት የማሽነሪ፣ የሌሎች መሳሪያዎችና የሰው ሃይል አቅርቦት እንደማያሟሉ፣ እንዲሁም ለተወሰኑ የሥራ አይነቶች የሥራ ተቋራጮችና የአማካሪዎች እጥረት /በተለይም የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ተቋራጮች እጥረት/ መኖሩን እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ የኮንትራክተሮችን አፈፃፀም በየጊዜው የሚገመገምበት አሰራር ባለመኖሩ ኮንትራክተሮች ከዚህ በፊት የነበራቸው አፈጻጸም ሳይረጋገጥ ፍቃዳቸው የሚታደስ መሆኑን ከሚ/ር መ/ቤቱ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እና በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

52. ስለ ሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የኮንትራት ማኔጅመንት ችግርን ለመፍታት እና የኮንትራክተሮች አቅም ለማሳደግ መንግስት መስራት ያለበት መሆኑን፣ ለዚህም አቅማቸውን ለመገንባት ኮሚቴ የተቋቋመ መሆኑን እንዲሁም ኮንትራክተሮችም ለስራ የሚያስፈልጋቸውን ማሽን መንግስት ገዝቶ እንዲያከራይላቸው ተጠይቆ ወደሥራ እየተገባ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

53. ሚ/ር መ/ቤቱ ለመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች መረጣ ብቃታቸው የተረጋገጠላቸውን እና አስፈላጊ መሣሪያዎች ያላቸውን ተቋራጮችን በማረጋገጥ ተፈጻሚ ማድረግ አለመቻሉ አቅም የሌላቸው ኮንትራክተሮች ተሰማርተው ሥራው በአግባቡ ተፈጻሚ እንዳይሆን እና ለፕሮጀክቶቹ የተመደበው ጊዜ እና በጀት እንዲባክን ያደርጋል፡፡

## የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የካሳ አከፋፈልን በተመለከተ፡-

54. ለመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶቹ አገልግሎት የሚስፈልጉ ቦታዎች በጥናት ሊለዩ ይገባል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 455/1997 መሰረት ለሥራው (ለጉድጓድ ቁፋሮ፣ ለመስመር ዝርጋታና ለግንባታ) የሚያስፈልገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ

መረጃ ቢያንስ ሥራው ከመጀመሩ ከአንድ አመት በፊት አዘጋጅቶ መሬት ለማስለቀቅ ስልጣን ላላቸው አካላት በመላክ ማስፈቀድ ይጠበቅበታል፡፡ መረጃው የደረሳቸው አካላትም ተገቢውን የካሳ ግምት በማውጣት እና ካሳ ሚከፈላቸውን አካላት በመለየት ካሳ እንዲከፈላቸው በማድረግ ቦታውን ለልማት ስራው ሊያስለቅቁ ይገባል፡፡

55. ለሥራው የሚያስፈልገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ መረጃ ቢያንስ ሥራው ከመጀመሩ ከአንድ አመት በፊት አዘጋጅቶ መሬት ለማስለቀቅ ስልጣን ላላቸው አካላት በመላክ ማስፈቀድ እንደሚገባው ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 455/1997 ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በአምስት ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት

- የውሃ ጉድጓድ የሚቆፈርባቸው፣ የሲቪል ሥራ የሚከናወንባቸው እና የውሃ ቧንቧ መስመር ዝርጋታ ለሚከናወንባቸው ቦታዎች የሚያስፈልገውን መሬት ለማስለቀቅ ፕሮጀክቱ ሥራ ከመጀመሩ አንድ አመት በፊት መሬቱን ለሚያስለቅቁ አካላት መረጃው እንዲደርሳቸው አለመደረጉን፣
- በሐዋሳ ጥቅምት 2007 ዓ.ም የተጀመረው የመስመር ዝርጋታ እስከ አሁን መጠናቀቅ ሲገባው በካሳ አከፋፈል ላይ በተከሰተ ችግር የመስክ ጉብኝት እስከ ተደረገበት (የካቲት 2008 ዓ.ም) ድረስ 4.7 ኪ.ሜ. የቧንቧ የመስመር ዝርጋታ እና የውሃ ብክነት ለመቀነስ ለሚደረግ የመስመር ቅየራ በሃዋሳ ከተማ የዋናው መንገድ ላይ በሚገኙ የነባር መስመሮች ቅየራ ያልተከናወነ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው የመስክ ጉብኝት ከተደረገባቸው እና መጠይቅ ከቀረበላቸው የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. ስለ ሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ፕሮጀክቱ ሲጀምር በድዛይን እና ጥናት መሰረት ሲሆን ጥናቱ የፕሮጀክቱ አካል ሲሆን ከጥናት በኃላ አንድ አመት ጊዜ ተወስዶ የካሳ ክፍያ ሂደት ማስፈፀም አለመቻሉን፣ የአካባቢ ተፅዕኖና የማህበረሰብ አሰስመንት ጥናት የተካሄደ ቢሆንም በመንግስት አዋጅ መሰረት መስራት ቢቻል የተሻለ መሆኑን እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በአጠቃላይ በፕሮጀክቱ የሚታዩ የካሳ ክፍያ ችግሮች በአከባቢው ከተማ አሰተዳደር መሆኑን፣ መንግስትም ከዓለም ባንክ ጋር በገባው ውል መሰረት ከብድርና ከዕርዳታ ገንዘብ ካሳ መክፈል የማይችል መሆኑን እና በዚህ ረገድ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምክርና የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ከመስጠት በላይ የዘለለ ኃላፊነት የሌለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ለውሃ አገልግሎቶቹ ተገቢው የክትትልና ድጋፍ

በማድረግ የተወሰነውን ችግር መቅረፍ ይቻል ስለነበረ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

57. ለሥራው የሚያስፈልገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ መረጃ ከአንድ አመት በፊት አስለቅቀው አለማጠናቀቃቸው የፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም እንዲጓተት አድርጎታል፡፡

## ሚ/ር መ/ቤቱ የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ስለመሆኑ፡-

58. ሚ/ር መ/ቤቱ የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ የውሃ ፈንድ፣ አለም ባንክ ከከተማ መስተዳድሮች፣ ከክልል ውሃ ቢሮዎች፣ ከውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች፣ ከኢቲዮ ቴሌኮም፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት) ጋር ወጥ የሆነ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

59. በከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ውስንነት መኖሩን እና በየስድስት ወር በዓለም ባንክና በሚ/መ/ቤቱ በሚካሄደው ግምገማ ላይ የቀድሞው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተሳትፎ አለመኖሩን፣ የውሃ ብክነት ለመቀነስ በከተሞች ውስጥ ለሚከናወኑ የነባር ቧንቧ መስመር ቅየራ በመብራት ኃይል፣ ከኢትዩ ቴሌኮም፣ እና ከመንገዶች ባለሥልጣናት ጋር የሥራ ትብብር ማነስ ምክንያት ያልተቀየሩ መስመሮች መኖራቸው ታውቋል፡፡

60. እንዲሁም በሀዋሳ ከተማ በፕሮጀክቱ የተከናወነው የውሃ አቅርቦት ለህብረተሰቡ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ለተቆፈሩት የውሃ ጉድጓዶች እንዲያገለግሉ ከሁለት ዓመት በፊት ለ9 ትራንስፎርመር ተከላ 4.2 ሚሊዮን ብር ለቀድሞው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የተከፈለ ቢሆንም ትራንስፎርመሮቹ እስካሁን ያልተተከሉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በተደረጉ በመስክ ጉብኝት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

61. እንዲሁም ለሐዋሳ ከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት በመጀመሪያው ዙር አምቦ ውሃ ምንጭ ከሚባለው አከባቢ የውሃ መስመር ወደ ከተማው ሲዘረጋ የአከባቢው ህብረተሰብ እንዲጠቀምበት ተብሎ የተሰሩ ሁለት ምንጭ (አንድ ባለ 15 ሊትር በሴኮንድ እና ባለ

5 ሊትር በሴኮንድ የሚሰጡ) የተዘጋጀ ቢሆንም ውሃው ጥቅም ላይ ሳይውል ታሽጎ የተቀመጠ መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡

62. ስለ ሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ከዚህ በፊት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርንም ሆነ የክልል የውሃ ቢሮዎችን በየስድስት ወሩ ስብሰባ ላይ እንዲሳተፉ የሚጠይቁዋቸው እንደነበር፣ ነገር ግን ብዙን ጊዜ ስለማይሳተፉ መጋበዝ የተው መሆኑን፣ ገንዘቡን የሚያስተዳድረው ሚ/ር መ/ቤቱ በመሆኑ በየ6 ወሩ ባይሆንም የፕሮጀክት ማራዘሚያ በሚጠየቅበት ጊዜና የተለያዩ ውይይቶች ላይ እንደሚሳተፉ የክልል ውሃ ቢሮዎችም በፊት የሚሳተፉ እንደነበር ነገር ግን የማይመጡ መሆኑን እንዲሁም የሴክተሩ ሪፖርት ሪቪው በየ6 ወሩ ከክልሎች እና ከተሞች ጋር ውይይት መደረጉን እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የከተሞች የመሰረተ ልማት መሪ ዕቅድ (Master Plan) በወቅቱ ባለመኖሩ፣ ባለመሻሻሉ እንዲሁም የከተማ አስተዳደር መሰረተ ልማት ከሚዘረጉ ተቋማት በቅርበት ተቀናጅቶ ባለመሰራቱ በውሃ መስመሮች ላይ ጉዳት መድረሱን፣ ሆኖም ውሃ አገልግሎቶቹም በካሳ መልክ የሚያገኙትን ገንዘብ ይህንኑ ችግር ለማቃለል የሚጠቀሙ መሆኑን ቢገልጹም ሚ/ር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መሥራት ስለሚጠበቅበት ያቀረቡት ምክንያቶች በቂ ሆነው አልተገኙም፡፡ በተጨማሪም የመብራት ኃይል አቅርቦትን በተመለከተ በአሁኑ ወቅት ለሃዋሳ ከአንድ ትራንስ ፎርመር በስተቀር ሁሉም ትራንስፎርመሮች መተከላቸውን እና ለጎንደር ከተማ የሚገለግሉትም ምርታቸው ተጠናቆ በመጓጓዝ ላይ እንደሚገኝ እና በአጠቃላይ ለውሃ ፕሮጀክቶች የኃይል አቅርቦት ቅድሚያ እንዲሰጣቸው እንዲደረግ መወሰኑን፣ ሚ/ር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ያለሥራ የተቀመጠውን የምንጭ ውሃ የአካባቢው ህብረተሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን እንደሚያደርጉ እንዲሁም ከክልሎች ጋራ በቅንጅት የመስራቱ ሁኔታ ከተሞቹ ተጠሪነታቸው ለክልል መስተዳድሮች በመሆኑ ይህ እንደ ክፍተት ታይቶ ለወደፊቱ ትኩረት ሰጥተውበት የሚሰሩ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

63. ሚ/ር መ/ቤቱ የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (ገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒሰቴር፣ የውሃ ፈንድ፣ አለም ባንክ ከከተማ መስተዳድር፣ ከክልል ውሃ ቢሮዎች፣ ከውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች፣ ከቀድሞው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር፣ ከኢቲዮ ቴሌኮም፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት) ጋር ወጥ የሆነ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ በሥራው ሂደት የሚፈቱ ማነቆዎች እንዳይፈቱ

በማድረግ ፕሮጀክቶቹ በታቀደላቸው ጊዜ እና በጀት እንዳይጠናቁ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡

## የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የሪፖርት ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፡-

64. ሚ/ር መ/ቤቱ የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ወጥ የሆነ የሪፖርት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

65. የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ክትትል ጋር ተያይዞ የክልሎች ሪፖርት የጥራት ችግር ያለባቸው በመሆኑ በፌዴራል ደረጃ ሪፖርት በወቅቱ ለማዘጋጀት ችግር መፍጠሩ፣ ሪፖርት ተሟልቶ በተጠየቀው ጊዜ አለመቅረቡን እንዲሁም ክልሎች ባላቸው አሰራር መሰረት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት አዘጋጅተው የሚያቀርቡበት እና በሚ/ር መ/ቤቱ ሪፖርት የሚፈለግበት ጊዜ አለመጣጣምና የሚቀርቡ ሪፖርቶችም የጥራት (የመረጃ መፋለስ) ችግር መኖርና ሙሉ አለመሆን (ዕቅድና ክንውን በተለይም ተጠቃሚን) አለማካተት የሚስተዋሉ ችግሮች መሆናቸውን ከሚ/መ/ቤቱ የ2005 ፣ 2006 እና 2007 በጀት ዓመት የፕሮግራም አፈጻጸም ሪፖርቶች በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

66. ለማሳያ ያህል በሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዳይሬክቶሬት የ2007 በጀት ዓመት የ6 ወር አፈፃፀም ሪፖርት መሰረት የሀዋሳ ከተማ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አጠቃላይ አፈጻጸም 71% መድረሱን የሚያመለክት ቢሆንም የሚ/ር መ/ቤቱ የ2007 በጀት አመት አፈፃፀም ሪፖርት በተመሳሳይ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም 65 በመቶ ላይ መድረሱን እንዲሁም በሀዋሳ ከተማ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት 2ኛ ሩብ ዓመት 2008 ዓ.ም አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚያመለክተው የፕሮጀክቱ አጠቃላይ አፈፃፀም 65% ላይ መድረሱን የሚያሳይ ቢሆንም የተለያዩ ማስረጃዎች የቀረቡ በመሆኑ ትክክለኛ ፕሮጀክቱ የደረሰበትን ደረጃ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

67. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ይህ ችግር የሴክተሩ ችግር መሆኑን፣ ፕሮጀክቶችን የሚከታተሉት በImplementation manual ላይ በተቀመጠው ሪፖርቲንግ ስርዓት መሆኑን፣ የውሃ አገልግሎቶች ተጠሪነት ለየክልላቸው ከተማ አስተዳደር ስለሆነ የራሳቸው አሰራር ስላላቸው ነው ብለዋል፡፡ የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜውም የተለያየ ስለሆነ መረጃ ለማግኘት በስልክና በኢ-ሜይል የሚጠቀሙ እና ይፋዊ መረጃ ስላልሆነ ታማኝነት እንደማይኖረው ችግሩን ለመፍታት ከነርሱ አቅም በላይ መሆኑን፣ እንዲሁም የሀዋሳን በተመለከተ አንድ ጊዜ የሲቪል

ምርክ ስራ በስህተት እንደ ፕሮጀክት አጠቃላይ አፈፃፀም የወሰዱበት ጊዜ እንደነበር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተጨማሪ ስራ በመጨመሩ የፕሮጀክቱ አጠቃላይ አፈፃፀም በፊት ከነበረው አፈጻጸም (አዲሶቹም ስለሚካተቱ) በፐርሰንት መቀነሱን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን የገለጹ ቢሆንም ሁሉም የከተማ ውሃ አገልግሎቶች በፕሮጀክት የአፈጻጸም ማንዋል በሚያስቀምጠው መሰረት ሪፖርት እንዲያደርጉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማድረግ ይጠበቅበት ስለነበረ እንዲሁም ሪፖርታቸውን ሲያስተካክሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያሳውቁበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይቻል ስለነበረ የተሰጠውን ምክንያቱን ለመቀበል ያዳግታል፡፡

68. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን በተመለከተ ወጥ የሆነ የሪፖርት ሥርዓት አለመዘርጋቱ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓቱ የላላ እንዲሆንና ትክክለኛ መረጃዎች በወቅቱ እንዳይቀርቡ አድርጓል፡፡

## የከተሞች የመጠጥ ውሃ የፕሮጀክቶች ግዥ ሥርዓትን በተመለከተ፡-

69. ለፕሮጀክቶቹ ለመሳሪያዎች እና እቃ፣ ለሥራዎች እና ከማማከር አገልግሎት ውጪ ለሆኑ አገልግሎቶች (non consulting services) ግዥ የቀጥታ የኮንትራት ውል አፈጻጸም (Direct contracting) ከአለም ባንክ የNo-objection (የማረጋገጫ) ምላሽ በወቅቱ እንዲሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ

- በሐዋሳ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት በሁለተኛው ፌዝ ወንዶ ገንት አከባቢ ለሚገኘው ለአምቦ ወሃ ምንጭ የመስመር ዝርጋታ የዲሲ አይ እና የፒቪሲ ቧንቧዎች ግዥ ለመፈጸም አቅራቢው ጨረታውን ያሸነፈው በብር ምንዛሬ በመሆኑ እና L/C የሚከፈተው በዶላር በመሆኑ ይህን ለማስታረቅ በመዘግየቱ ብቻ 1 ዓመት ከስድስት ወር የፈጀበት ሁኔታ መኖሩን፣
- የድሬዳዋ ከተማ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት በ2006 ዓ.ም የወጣው የቧንባ ግዥ ጨረታን በተመለከተ የሎት-1 ድሲ አይ ፓይፕስ እና ፍቲንግ እና የሎት-2 ዩፐቪሲ ፓይፕስ እና ፊቲንግ አቅርቦት የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ መስከረም 20 ቀን 2006 ዓ.ም ሲሆን የሎት 1 ድሲ አይ ፓይፕስ እና ፊቲንግ አቅርቦት ከ18 ወራት መዘግየት በኃላ የካቲት 26 2007 ዓ.ም ኮንትራት የተፈረመ እና የሎት 2 ዩፒቪሲ ፓይፕስ እና ፊቲንግ አቅርቦት ኮንትራት የተፈረመው በሐምሌ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ቢሆንም ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተው የካቲት 26 2007

ዓ.ም መሆኑን፣በድሬዳዋ የሎት 1 ፓይፕ ዝርጋታ ስራ አዋሽ ወልዴ ጀነራል ኮንትራክተር ጨረታውን አሸንፎ ከ7 ወራት በኃላ የውል ስምምነት መፈረሙን እና በድሬደዋ አዋሽ ወልዴ ጄኔራል ኮንትራክተር አፈጻጸም ሪፖርት እንደሚያመለክተው የዲሲ አይ ቧንቧ እና የፊቲንጎች ውል ዘግይቶ የተፈረመ በመሆኑ እስከ March 5, 2015 የቧንቧው ዝርጋታ ያልተከናወነ መሆኑን፣

- የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግዥ አፈጻጸም በግዥ እቅድ፣ በመንግስት ግዥ መመሪያ እና በአለም ባንክ የግዥ መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ቢሆንም የጨረታ ሂደት ላይ ይሁንታ (No-objection) ለማግኘት እስከ ስድስት ወር ሚ/ር መ/ቤቱ ላይ የሚቆይበት ሁኔታ መኖሩን እና ሚ/ር መ/ቤቱ የገበያ ዋጋ ዝርዝር ጥናት ስለሌለው የውሃ አገልግሎቶቹ በራሳቸው ገበያ አንዲያጠኑ ስለሚደረግ ጊዜ የሚወስድበት ሁኔታ በመኖሩ በፕሮጀክቱ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የድሬደዋ እና ሐዋሳ የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

71. ስለጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የግዥ ባለሙያ እጥረት እና ልምድ ችግር መኖሩን፣ ከዲዛይን ሪቪው ጋር ተያይዞም የሚፈጠሩ ጉዳዮች መኖራቸውን፣ የዋጋ ዝርዝር ጥናት ከዕቅድ ጋር ተያይዞ ወቅታዊ የገበያ ሁኔታ ለማወቅ ይረዳል ነገር ግን የማይመከር መሆኑን በአጠቃላይ ችግሩ ከዲዛይን ጀምሮ የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ጋር ተያይዞ አቅም ውስንነት ያለ መሆኑን እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የድሬደዋ ሎት 1 የቧንቧ ዝርጋታ ሥራ ተጫራቹ ከተለየ በኋላ ውል መፈራረሙ ለ7 ወራት የቆየበት ዋናው ምክንያት ፀረ- ሙስና ኮሚሽን የቧንቧ አቅርቦት ጨረታ ሂደቱ እስኪጣራ ድረስ እንዲቆም በመደረጉ መሆኑን፣ ወዲያውኑ ውል ቢፈረም ዕቃውን ማቅረብ ስለማይቻል እንዲዘገይ የተደረገ መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡

72. ለፕሮጀክቶቹ ለመሳሪያዎች እና እቃ፣ ለሥራዎች እና ከማማከር አገልግሎት ውጪ ለሆኑ አገልግሎቶች (non consulting services) ግዥ የቀጥታ የኮንትራት ውል አፈጻጸም (Direct contracting) ከአለም ባንክ የNo-objection (የማረጋገጫ) ምላሽ በወቅቱ እንዲገኙ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢው ድጋፍ አለመሰጠቱ ፕሮጀክቶቹ እንዲጓተቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## በከተሞች የሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የመሳሪያ እና የተለያዩ ንብረቶች ግዥ በውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ፡-

73. በከተሞች የሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የመሳሪያ እና የተለያዩ ዕቃዎች (የፓይፕ፣ የኤሌክትሮሚካኒካል...) ግዥ ሲፈጸም የተገዙት ንብረቶች በስፔስፊኬሽኑ (specification) መሰረት ጥራታቸውን ጠብቀው መገዛታቸውን በሚመለከተው ባለሙያ ተረጋግጦ በውሉ መሰረት ተፈጻሚ ሊደረግ ይገባል፡፡

74. ይሁን እንጂ በሐዋሳ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ወንዶ ገነት አከባቢ ለሚገኘው ለአምቦ ወሃ ምንጭ የመስመር ዝርጋታ የፒቪሲ እና የዲሲ አይ ቧንቧ ጨረታ ሂደትን በሚመለከት በዓለም አቀፍ ደረጃ የቻይና አምራች አሸናፊ ሆኖ ዕቃውን ጅቡቲ ወደብ ካደረሰ በኋላ ዕቃዎቹን ከጅቡቲ ወደ ፕሮጀክት ሥፍራው እራሱ ማድረስ ሲገባው የውሃ አገልግሎቱ እንደ አቅራቢው ሆኖ እንዲያጓጉዝ በማለቱ፣ የመጓጓዝ ሂደቱ ላይ የውሃው አገልግሎቱ ለማጓጓዝ ልምድ የሌለው በመሆኑ ማጓጓዝ በመዘግየቱ እና የመጡት ዕቃዎች ለ5 ወራት በጅቡቲ በመቆየታቸው ፕላስቲክ የሆኑት ፕሮጄክቱ ሥፍራ ከደረሱ እና ከተገጣጠሙ በኋላ በጸሃይ በመጎዳታቸውና በመፈነዳታቸው የውሃ አገልግሎቱ ከራሱ መደበኛ በጀት ከሀገር ውስጥ አምራቾች በመግዛት ለመተካት የተገደደ በመሆኑ ተጨማሪ 3.5 ሚሊዮን ብር ወጪ ያደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ እንዲሁም አቅራቢው በውሉ መሰረት እንዲያጓጉዝ አለመደረጉ እና ዕቃዎቹን ከወደብ በአፋጣኝ አንስቶ ወደ ውሃ አገልግሎቱ በማጓጓዝ ሂደት ውስጥ የሚ/ር መ/ቤቱ ድጋፍ እንዲኖር አለመደረጉና ሚንስቴር መ/ቤቱ አቅራቢውን በመከታተል ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት አለማድረጉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጦ ቃለ መጠይቅ ከቀረበለት የሀዋሳ ውሃ አገልግሎት ለመረዳት ተችሏል፡፡

75. ስለጉዳዩ የሚንስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በአቅርቦት ላይ ያለው ችግር አለም ዓቀፋዊ ስለሆነ በመተማመን እና ስምምነት ብቻ የሚከናወን በመሆኑ እቃው ሳይታይ በቀረቡ ማስረጃዎች ላይ ብቻ ውል በመፈጸም 90 በመቶ ክፍያ ስለሚፈፀም ኢንሹራንስ የሌለው መሆኑን፣ ሀዋሳ ያጋጠመው ችግር ደግሞ ከዚህ ሌላ የአቅራቢው የመጀመሪያው performance security expired ማድርጉን፣ አቅራቢው ንብረቶቹን እስከ ሀዋሳ ማምጣት እንደነበረበት ነገር ግን ሳያመጣ ቀርቶ በጅቡቲ ስለ ጣለ የከተማው ውሃ አገልግሎት በቀሪ 10 ፐርሰንት ብር ዕቃውን እንዲያስገባ መደረጉን ነገር ግን የተበላሹ ወይም የፈነዳዱ ንብረቶች መኖራቸውን እና

መግዛታቸውን መረጃ የየሌላቸው መሆኑን እና እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያይዞ ውሃ አገልግሎቱም ድጋፍ አለመጠየቁን፣ በተጨማሪም ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ፣ ችግሩ የነበረሲሆን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ ትራንዚተር ቀጥሮ እንዲያጓጉዙና ቀሪ ለአቅራቢ ያልተከፈለ ገንዘብ እንዲያገኙ አስፈላጊው ድጋፍ መደረጉን እና በወቅቱ ለቻይና ኤንባሲ የቅሬታ ደብዳቤ የጻፉ መሆኑን ቢገልጹም ክትትል በማድረግ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ስለሚጠበቅባቸው የሰጡትን ምላሹ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

76. የመሳሪያ እና የተለያዩ ዕቃዎች (የፓይፕ…) ግዥ ሲፈጸም በውሉ መሰረት በአግባቡ ተጠብቆ ከቦታው እንዲደርስ አለመደረጉ ተገዝተው የመጡ ንብረቶች ለብክነት እንዲጋለጡ አድርጓል፡፡

## የአቅም ግንባታ እንዲሁም የስልጠና ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፡-

77. ሚንስቴር መ/ቤቱ በፕሮጄክቶቹ ፋይናንስና ፕሮኩርመንት (ግዥ) አሰራር፣ የኤሌክትሮሜካኒካል እና የኮንትራት ማኔጅመንት ሥራዎችን በተመለከተ የአቅም ግንባታና ስልጠና ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡

78. ሚንስቴር መ/ቤቱ የፕሮኩርመንት፣ የኤሌክትሮሜካኒካል እና የኮንትራት ማኔጅመንት ሥራዎችን በተመለከተ ለውሃ አገልግሎቶች እነርሱ በሚፈልጉት ደረጃ ድጋፍ የማይሰጣቸው መሆኑን፣ በከተማ ውሃ አገልግሎቶች የሚከናወኑ የግዥ ግምገማዎች የግዥ መመሪያውንና የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ ባለመረዳት ምክንያት በትክክል ሳይሰሩ ለሚንስቴር መ/ቤቱ ሲያቀርቡ የማስተካከያ አስተያቶች እንደሚሰጡ፤ በዚህ ሂደት የጊዜ መጓተት የሚከሰት መሆኑን፣ የግዥ ግምገማዎች የግዥ መመሪያውንና የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ ለመረዳት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥራ እንዲከናወን አለመደረጉን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሉት ባለሙያዎች ከአምስት ከተሞች የመጠዋ ውሃ በተጨማሪ ሌሎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከናውናቸውን ፕሮጄክቶች ጭምር የሚሰሩ መሆኑን በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው ከታዩ የውሃ አገልግሎቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

79. ስለ ጉዳዩ የሚንስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ባለሙያ ከዚህ በፊትም እንደነበራቸው አሁንም 3 ባለሙያዎች መኖራቸውን፣ የግዥ ባለሙያ ከዚህ በፊት አንድ እና ሁለት ባለሙያ የነበሩበት ጊዜ ቢኖርም አሁን ግን ከአንድ አመት በፊት የተቀጠሩት 6 የግዥ ስፔሻልስቶች ያሉዋቸው መሆኑን እንዲሁም የኤሌክትሮሜካኒካልም የተፈቀደላቸው 2 ባለሙያ ቢሆንም አሁን ያለው

ግን አንድ ባለሙያ ብቻ ያላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በፕሮጀክቱ ስምምነት መሰረት ተገቢውን ባለሙያ መቅጠር ያለባቸው ቢሆንም ለምሳሌ የግዥ ባለሙያ ከጎንደር እና ከድሬዳዋ ከተማ የውሃ አገልግሎቶች በስተቀር ሌሎቹ ያልቀጠሩ በመሆኑ፣ ሥልጠና ሳይሰጥ ቀርቶ ሳይሆን የወሰዱት ሰዎች እየለቀቁ በመቸገራቸው መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

80. ለፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ፈንድ በወቅቱ አለመለቀቅ፣ በፋይናንስና ፕሮኩርመንት (ግዥ) አሰራር፣ የኤሌክትሮሜካኒካል እና የኮንትራት ማኔጅመንት ሥራዎችን በተመለከተ ተሰጡ የተባሉት ስልጠናዎቹ ተግባር ላይ ባለመዋላቸው ሥራውን በአግባቡ እንዳይወጡት በማድረግ የፕሮጀክቶቹ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዳይጠናቀቁ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

81. ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው የአምስት ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ በሚ/ር መ/ቤቱ እና በናሙና ተመርጠው በታዩት የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች የታዩ ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡-

- የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ከመጀመራቸው በፊት ፕሮጀክቱ የሚፈጥረው አካባቢ ተፅዕኖ እና ሌሎች ጉዳዮች ጥናት ውስጥ የሚካተቱ ቢሆንም ወደ ተግባር የማይለወጡ መሆኑን፣
- በከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ዲዛይን በተደጋጋሚ ክለሳ የሚደረግባቸውና አንዳንዶቹ ክላሳዎች ውሳኔ ለማግኘት ረጅም ጊዜ መውሰዳቸውና ፕሮጀክቶች መጓተታቸው፣
- የአምስቱ ከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የተያዙ ስራዎቸ በተያዘላቸው የጊዜ ገድብ ያልተጠናቀቁ መሆኑን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ተገቢውን ቁጥጥር እና ክትትል ስርዓት በመዘርጋት የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም መከታተል አለመቻሉ፣
- ኮንትራክተሮች በገቡት ውል መሰረት የማያከናውኑ እና የሥራ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑ፣ የፕሮጀክት አስተዳደር አጥጋቢ አለመሆኑ፣ ሥራ ተቋራጮች ውል ከፈጸሙ በኃላ ቶሎ ወደ ስራ እንዲገቡ የማይደረግ መሆኑ፣ ሥራውን በውላቸው መሰረት በማያከናውኑ ተቋራጮች ላይ በውሉ መሰረት አስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ፣
- በሥራ ተቋራጮች በኩል ሁሉንም ቅድመ ሁኔታ እናሟላለን ብለው ጨረታ አሸንፈው ውል ከገቡ በኋላ የሚታይ የማሽነሪ፣ የሌሎች መሳሪያዎችና የሰው ሃይል በገቡት ውል መሰረት የማያቀርቡ መሆኑ፣ ሚንስቴር መ/ቤቱ የኮንትራክተሮችን አፈፃፀም በየጊዜው የሚገመግምበት አሰራር ባለመኖሩ ኮንትራክተሮች ከዚህ በፊት የነበራቸው አፈጻጸም ሳይረጋገጥ ፍቃዳቸውን የሚያድስ መሆኑ፣
- በአምስት ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የውሃ ጉድጓድ የሚቆፈርባቸው፣ የሲቪል ሥራ የሚከናወንባቸው እና የውሃ ቧንቧ መስመር ዝርጋታ ለሚከናወንባቸው ቦታዎች የሚያስፈልገውን መሬት ለማስለቀቅ ፕሮጀክቱ ሥራ

ከመጀመሩ አንድ አመት በፊት መሬቱን ለሚያስለቅቁ አካላት መረጃው እንዲደርሳቸውተደርጎ የካሣ ክፍያ እንዲከናወን አለመደረጉ፣

- በከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በሚደረገው በየስድስት ወር በዓለም ባንክና በሚ/መ/ቤቱ በሚካሄደው ግምገማ ላይ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና የክልል የውሃ ቢሮዎች የማይሳተፉ መሆኑ፣
- የውሃ ብክነት መስመር ዝርጋታ በመብራት ኃይል፣ በቴሌ፣ እና በመንገድ ሥራ ትብብር ማነስ ምክንያት ያልተቀየሩ መስመሮች መኖራቸው እና በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቶች መጓተታቸው፣ እንዲሁም በሀዋሳ ከተማ በፕሮጀክቱ የተከናወነው የውሃ አቅርቦት ለህብረተሰቡ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ከሁለት ዓመት በፊት ለ9 ትራንስፎርመር ተከላ 4.2 ሚሊዮን ብር ለቀድሞው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የተከፈለ ቢሆንም ትራንስፎርመሮቹ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ያልተተከሉ መሆኑን፣
- የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ክትትል ጋር ተያይዞ የክልሎች የሚያቀርቡት ሪፖርት እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያጠናቅረው ሪፖርት የማይናበቡ መሆኑን፣
- የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግዥ አፈጻጸም የጨረታ ሂደት ላይ ይሁንታ (No-objection) ለማግኘት እስከ ስድስት ወር ሚንስቴር መ/ቤቱ ላይ የሚቆይበት ሁኔታ መኖሩን፣ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመጠጥ ውሃ በየጊዜው እራሱም ሆነ ከተሞች ለሚያከናውናቸው ግዥዎች የሚያገለግል የገበያ ዋጋ ዝርዝር መረጃ የሌለው መሆኑ፣
- በሐዋሳ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ወንዶ ገነት አከባቢ ለሚገኘው ለአምቦ ወሃ ምንጭ የመስመር ዝርጋታ የፒቪሲ እና የዲሲ አይ ቧንቧ ጨረታ ሂደትን በሚመለከት በዓለም አቀፍ ደረጃ ጨረታውን ያሸነፈው የቻይና አምራች ኩባንያ ከውሉ ውጭ ዕቃዎቹን ጅቡቲ ወደብ ላይ ያራገፈ እና የመጡት ዕቃዎች ለ5 ወራት በጅቡቲ በመቆየቱ የተበላሹ በመሆናቸው የከተማውን ውሃ አገልግሎት በጀት ከሀገር ውስጥ አምራቾች በመግዛት ለመተካት የተገደደ በመሆኑ ተጨማሪ 3.5 ሚሊዮን ብር ወጪ እንዲወጣ የተገደደ መሆኑ፣ ሚንስቴር መ/ቤቱ አቅራቢው ላይ በመከታተል ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት አለማድረጉ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮኩርመንት፣ የኤሌክትሮሜካኒካል እና የኮንትራት ማኔጅመንት ሥራዎችን በተመለከተ ለውሃ አገልግሎቶች አስፈላጊውን ድጋፍ የማይሰጣቸው መሆኑን፣

82. በአጠቃላይ የአምስቱ ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ሚ/ር መ/ቤቱ ትኩረት በመስጠት አስፈለጊውን ድጋፍ አለማድረጉ፣ የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ ከላይ የተጠቀሱት ግኝቶች እንዲፈጠሩ አስችሏል፡፡ ስለሆነም የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚ/ር ከሌሎች ባለድርሻ አካለት ጋር በመቀናጀት ለፕሮጀክቶቹ አስፈላጊውን ድጋፍ አለመስጠቱ ፕሮጀክቶቹን ከግብ ለማድረስ እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል ከላይ የተጠቀሱትን ድክመቶች እና ግድፈቶች በብቃት፣ ኢኮኖሚ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ የአምስቱን ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀም ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

- የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ለጥናቱ ያወጡት ወጪ እንዳይባክን እና ለተጨማሪ ወጪ እንዳይዳረጉ ለማስቻል ለከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ትግበራ የፕሮጀክት የአዋጭነት ( Feasibility study)፣ ፕሮጀክቶች ለምን ያህል ጊዜ (project time)፣ ህዝብ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው የሚያመለክት እና ፕሮጀክቱ የሚፈጥረው አካባቢ ተፅዕኖ እና ሌሎች ጉዳዮች ሊካተቱና በጥናቱም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም ተግባራዊነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክቶቹን በታቀዱት አግባብ ለመምራት በከተሞች የሚገኙ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች፣ ጥናትና ዲዛይን ሊጠናቀቅ፣ አስፈላጊ ሆኖ ክለሳም ሲከናወን የፕሮጀክቶቹ ሥራ እንዳይጓተት በአፋጣኝ በየደረጃው በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግሞ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያስተባብራቸው የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች የውሃ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተደራሽነትን በወቅቱ እንዲያድግ ለማድረግ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ኮንትራት አስተዳደር በተገባው የኮንትራት ውል ስምምነት መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ ለመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች መረጣ ብቃታቸው የተረጋገጠላቸውን እና አስፈላጊ መሣሪያዎች ያላቸውን ተቋራጮችን በማረጋገጥ ተፈጻሚ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም ለአማካሪዎች በየወሩ የሚከፈለው ክፍያን በማስቀረት ልክ ለተቋራጮቹ እንደሚከፈለው በተሠራው ሥራ ልክ የሚከፈልበት የአሰራር ሥርዓት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የፕሮጀክቶቹ ሥራ እንዳይጓተት ለማድረግ ለሥራው የሚያስፈልገውን መሬትና መሬቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ መረጃ በቅድሚያ ተዘጋጅቶ መሬት ለማስለቀቅ ስልጣን ላላቸው አካላት በመላክ ማስፈቀድ እና ተገቢው የካሳ ክፍያ እንዲከፈል በማድረግ ሥፍራዎቹን ለሥራ ዝግጁ እንዲሆኑ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀምን ለማሳደግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ የውሃ ፈንድ፣ አለም ባንክ ከከተማ መስተዳድር፣ ከክልል ውሃ ቢሮዎች፣ ከውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች፣ ከኢቲዮ ቴሌኮም፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት) ጋር ቀጣይነት ያለው ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን ክትትል ለማድረግ በፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ማንዋል ላይ በተቀመጠው መሰረት የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓቱን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ለፕሮጀክቶቹ ለመሳሪያዎች እና እቃ፣ ለሥራዎች እና ከማማከር አገልግሎት ውጪ ለሆኑ አገልግሎቶች (non consulting services) ግዥ የቀጥታ የኮንትራት ውል አፈጻጸም (Direct contracting) ከአለም ባንክ የማረጋገጫ (No-objection) ምላሽ በወቅቱ እንዲሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሚገዙ ንብረቶችን ጥራት ለማስጠበቅ ይቻል ዘንድ በከተሞች የሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የመሳሪያ እና የተለያዩ ዕቃዎች (የፓይፕ…) ግዥ ሲፈጸም የተገዙት ንብረቶች በስፔስፊኬሰሽኑ (specification) መሰረት ጥራታቸውን ጠብቀው መገዛታቸውን በሚመለከተው ባለሙያ ተረጋግጦ በውሉ መሰረት ተፈጻሚ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በተደጋገሚ ለሚገዙ ዕቃዎች የገበያ ዋጋ መረጃ ሊያዘጋጅ እና ለሁሉም አስፈላጊ የሆኑትን ዕቃዎችና ግብዕቶች በማዕከላዊነት በማዕቀፍ የሚገዙበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ሚንስቴር መ/ቤቱ ለክልል ቢሮዎች ለፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ፈንድ በወቅቱ እንዲለቀቅ እና አፈፃፀሙን ለማሳደግ በፋይናንስና ፕሮኩርመንት (ግዥ) አሰራር፣ የኤሌክትሮሜካኒካል እና የኮንትራት ማኔጅመንት ሥራዎችን በተመለከተ ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡

83. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በታዩ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች እና የውሃ ፈንድ ልማት ጽ/ቤት የሚፈለጉ መረጃዎችን በማቅረብ እና ለቀረቡ ቃለ-መጠይቆች በወቅቱ መልስ በመስጠት ለተደረገልን የሥራ ትብብር ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

# አባሪ- 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| ተ.ቁ | የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ<br>Audit Issues | የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች<br>Evaluative Criteria |
|---|---|---|
| 1 | **የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ጥናት፤ዲዛይንእና ግንባታ ተሟልቶ መዘጋጀቱንና ብቃት ያለው የኮንትራት አስተዳደር ስርአት ተዘርግቶ መተግበሩን ማጣራት፤** | 1. ለከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ትግበራ የፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት (Feasibility study) ሊከናወንና በጥናቱም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | | 2. በከተሞች ለሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮክቶች ዝርዝር ዲዛይን ሊከናወንላቸው እና ሊከለሱ (Review) ይገባል፡፡ |
| | | 3. በከተሞች የሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ለምን ያህል ጊዜ (project time) እና ህዝብ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው በጥናት ውስጥ ሊያካትቱ ይገባል፡፡ |
| | | 4. በከተሞች የሚገኙ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች፣ ጥናትና ዲዛይን ተጠናቆ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | | 5. በከተሞች የሚገኙ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ለመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች መሟላት አለባቸው፤፤ |
| | | 6. የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ግንባታው በጥናትና ዲዛይን መሰረት እየተከናወነ ስለመሆኑ አግባብ ባለው ባለሙያ በመመደብ በየደረጃው ቋሚ ክትትል መደረግ አለበት፤ |
| | | 7. የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ኮንትራት አስተዳደር በተገባው የኮንትራት ውል ስምምነት መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | | 8. ለፕሮጀክተቶች ግንባታ የስራ ተቋራጮች ክፍያ በተቆጣጣሪ ማህንዲሱ በሚዘጋጀው የስራ ክንውን በሚያሳይ የክፍያ ሰርትፍኬት መሰረት መሆን አለበት፡፤ |
| | | 9. ሚ/መ/ቤቱ ከውጭ በሚገኝ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች |

| | | |
|---|---|---|
| | | ግንባታ በተቀመጠለት ጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ መከታተልና ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | | 10. ሚ/መ/ቤቱ በየጊዜው የአፈጻጸም ሪፖርቶችን በመገምገምና ግብረ መልስ በመስጠት፣ የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በቅርበት መከታተል አለበት፡፡ |
| | | 11. ሚኒስትር መ/ቤቱ በውጭ እርዳታ /ድጋፍ የሚሰሩ እና በፌዴራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ሂሳብ አፋጻጸምን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | | 12. ለመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ትግበራ እና አፈጻጸም የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ሊኖርና ተግባሪዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | | 13. ሚኒስትር መ/ቤቱ በከተሞች ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት የውሃ ተቋማትን የሚያስተዳድርበት መመሪያ (ጋይድላይን) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | | 14. ሚኒስትርመ/ቤቱ የመጠጥ ውሃ ግንባታ እና አቅርቦትን በተመለከተ የፕሮጀክቶች እቅድ አፈፃፀምም ባዘጋጀው የስትራቴጂክ እቅድ መሰረት መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | | 15. እያንዳንዱ የከተማ የውሃ አገልግሎት ቢሮ ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የተለየ የባንክ አካውንት ሊከፍት ይገባል፡፡ |
| 2 | **ለከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዋና ፈጻሚ ከሆኑ ባለድርሻ አካላት (የክልል ቢሮዎች፣** | 16. ሚ/መ/ቤቱ የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (ገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒሰቴር፤የውሃ ፈንድ፤አለም ባንክ |

| | | |
|---|---|---|
| | የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር፣የውሃ ፈንድ፤አለም ባንክ )- ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ስርአት የተዘረጋለት እና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ማጣራት፣ | ከከተማ መስተዳድር፣ ከክልል ውሃ ቢሮዎች ከውሃ አገልግሎት ጽ/ቤቶች) ጋር ወጥ የሆነ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 17. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት እቅድ ሲዘጋጅ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መለኩ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | | 18. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፕሮጀክቶች ግንባታ ለሚመለከተቸው ባለድርሻ አካላት የውይይትና የምክክር መድረክ ማዘጋጀት አለበት፡፡ |
| 3 | የከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግዥ አፈጻጸም በግዥ እቅድ፤በመንግስት ግዥ መመሪያ እና በአለም ባንክ የግዥ መመሪያ መሰረት መሆኑን ማጣራት፤ | 19. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለፕሮጀክቶች የባለሙያ አማካሪና ለኮንትራክተር አገልግሎት ግዥ እንዲሁም የእቃና መሳሪያዎች ግዥ ሲፈፀም በባንክ የግዥ መመሪያ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | | 20. ሚ/መ/ቤቱ የከተሞች ግዥ ኮሚቴዎች አቅም ለማጎልበት አስፈላጊውን የቴክንክ (ሙያዊ ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡ |
| | | 21. ሚ/መ/ቤቱ ለክልል ቢሮዎች (ለከተሞች ዩቲሊቲዎች) የጨረታ ግምገማ ሂደት መመሪያ ማዘጋጀት እና ሥራ ላይ ማዋል አለበት፡፡ |
| | | 22. በከተማ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ሥር ያሉ የተለያዩ የሲቪል ወርክ፣ የቁፋሮ የኢንስታሌሽን ሥራዎች እና የፓይፕ እና የተለያዩ መሣሪያዎች ግዥ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | | 23. ለከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ለስራ ተቋራጮች፣ አማካሪ ድርጅቶች የእቃ አቅራቢዎች የጨረታ አሰጣጥ ሂደት በአለም ባንክ የግዢ መመሪያ መሠረት እና በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ለአሸናፊ ድርጅቶች ሊሰጥና ውል ሊፈረም ይገባል፡፡ |
| | | 24. ለመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የሥራ ተቋራጮች መረጣ ብቃታቸው የተረጋገጠላቸውን እና አስፈላጊ መሣሪያዎች ያላቸውን ተቋራጮችን በማረጋገጥ ተፈጻሚ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 25. በከተሞች የሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የመሳሪያ እና የተለያዩ ዕቃዎች (የፓይፕ...) ግዢ ሲፈጸም የተገዙት ንብረቶች በስፔስፊኬሽኑ (specification) መሰረት ጥራታቸውን ጠብቀው መገዛታቸውን በሚመለከተው ባለሙያ የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት ሊኖር እና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፣ |
| | | 26. በክልል ከተሞች የሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የታደሰ ፍቃድ በተሰጣቸው ኮንትራክተሮች ሊገነቡ ይገባል፡፡ |
| | | 27. ሚ/መ/ቤቱ ለክልል ቢሮዎች ለፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ፈንድ በወቅቱ እንዲለቀቅ አፈፃፀምን በተመለከተ በፋይናንስና ፕሮኩርመንት(ግዥ) አሰራር ላይ ስልጠና መስጠትና የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡ |
| | | 28. ለፕሮጀክቶቹ ለመሳሪያዎች እና እቃ፣ ለሥራዎች እና ከማማከር አገልግሎት ውጪ ለሆኑ አገልግሎቶች ( non consulting services) ግዢ የቀጥታ የኮንትራት ውል |

| | | |
|---|---|---|
| | | አፈጻጸም (Direct contracting) ከአለም ባንክ የ No-objection(የማረጋገጫ) ምላሽ ሊሠጠው ይገባል፡፡ |
| | | 29. ሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱም ሆነ የክልል ቢሮዎች ለመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ከነባሩ ውል ለተጨማሪ ሥራዎች አቅርቦቶች (እቃዎች) እና ከምክር አገልግሎት ውጪ የሆኑ ሌሎች አገልግሎቶች( non consulting services) በሚያስፈልጉበት ጊዜ በነበረው ውል መሠረት አቅርቦቱ ሊራዘም የሚችለው ተጨማሪ ውድድር ቢደረግ የሚገኝ ጥቅም አለመኖሩን እና የተራዘመው የኮንትራት ውል ያለው ዋጋ ( price) አጥጋቢ(ተመጣጣኝ) reasonable መሆኑን የአለም ባንክ ሲያምንበት እና በነባሩ ውል ስለሁኔታው በቅድሚያ የተገለጸ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | | 30. የፕሮጀክቶች አፈፃጸም ሂደት የግንባታ ስራ የዋጋ ማስተካከያ ተግባሪዊ ሊደረግ የሚችለው የግንባታ ሥራውን ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ ከ18 ወራት በላይ ሲሆን እና ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከ12 ወራት በኋላ መሆን ይገባል፡፡ |